**የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን (WMATA)**

**Washington Metropolitan Area Transit Authority (WMATA)**

# የሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ 2017-2020

## *ማጠቃለያ*

## መነሻ

የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን (WMATA) በትራንዚት-ተኮር ሕዝባዊ ተሳትፎ፣ ትብብር እና ግንኙነት ለማካሄድ በትጋት ይሠራል፡፡ የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) ከፍተኛ ጥራት ያለው የሁለት-መስመር ግንኙነትን፣ በታቀዱት ፕሮጀክቶች ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ሁሉ ምላሽ ለመስጠት እና የፌደራል ግዴታዎችን ለማሟላት የሚያስችል መመሪያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

እንደ የፌደራል ገንዘብ ተቀባይ እንደመሆኑ እና በ1964 የህዝብ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 6 መሠረት፣ WMATA በዕቅዱ እና የፕሮግራም እንቅስቃሴዎቹ አናሳ እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን (LEP) የሚያሳትፍ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድና ስትራተጂ ዝርዝር ለፌደራል ትራንዚት አስተዳደር (FTA) ማቅረብ አለበት። ምንም እንኳን ይህ ዕቅድ የሚዘጋጀው የአንቀጽ 6 አስፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ቢሆንም፣ መዋቅሩ የተዘጋጀው "አስፈላጊ" ሆነ አልሆነ በሁሉም የባለሥልጣኑ ጥረቶች ላይ ተደራሽ እንዲሆን ነው።

የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የባለሥልጣኑን ፍልስፍና ለህዝብ ተሳትፎ፣ ትክክለኛነት፣ እና የላቀ የህዝብ አገግሎት የሚያንፀባርቁ መሪ መርሆዎች፣ ግቦች እና ዓላማዎች አዘጋጅቷል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን ለሚያነሳሱ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል አለባቸው፡፡

## የመመሪያ መርሆች

የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የባለሥልጣኑን ፍልስፍና ለህዝብ ተሳትፎ፣ ትክክለኛነት፣ እና የላቀ የህዝብ አገግሎት የሚያንፀባርቁ መሪ መርሆዎች፣ ግቦች እና ዓላማዎች አዘጋጅቷል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን ለሚያነሳሱ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል አለባቸው፡፡

### የ WMATA’s ለህዝብ ተሳትፎ አራት የመመሪያ መርሆች

**ሁሉን የሚያካትት**

በሕዝብ ተሳትፎ ሂደት ውስጥ ተጽዕኖ ሊያደርስባቸው የሚችል የሁሉንም ማህበረሰቦች ተሳትፎን በንቃት ማመቻቸት።

**ተባባሪ**

በዕቅድና በፕሮጀክት ልማት ሂደቱ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ መሥራት።

**ምላሽ ሰጪ**

እምነትን ለመገንባት የህዝብ አስተያየትን ከውጤቶች ጋር ማገናኘት፡፡

**ወጥ የሆነ**

ከህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ውስጥ የተገኙ መመሪያዎች በ WMATA ውስጥ መከተላቸውን ማረጋገጥ።

## የ PPP ፕሮጀክት ግንኙነት እና የስምሪት ዕቅድ

ከመጀመሪያው የ PPP ህትመት ኢና ከባለድርሻ አስተያየት በመነሳት WMATA በአሁኑ ጊዜ መደበኛ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ሂደት አዘጋጅቷል። ይህንን ሂደት በመከተል ለሁሉም የታቀዱ የፕሮጀክት ግንኙነቶች እና ስምሪት ዘዴዎች ተገዢነት እና ወጥነት ይረጋገጣል።

WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን የሚያነሳሱ የተለያዩ ፕሮጀክቶች እና እርምጃዎች አሉት። በአጠቃላይ፣ የደንበኞች ተጽዕኖ ያለው ወይም አስተያየት የሚጠይቅ ማንኛውም የታቀደ ፕሮጀክት የ PPP መመሪያዎችን መከተል አለበት።

የተቀላጠፈና ወቅታዊ የ PPP ሂደትን ለማረጋገጥ የ WMATA የውጭ ግንኙነት ቢሮ ከሌሎች ኢጋር ቢሮዎች ጋር

ከዲፓርትመንቱ ፕሮጀክት አስተዳዳሪዎች እና ተጠሪዎቻቸው ጋር ይሠራል። ይህም ወሳኝ የፕሮጀክት መረጃን፣ ወሰን/የጊዜ ሰንጠረዥን፣ ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ህዝቦች ስነ-ህዝብ መረጃዎች፣ የበጀት እና የግንኙነት እና የግባአት ዓላማዎችን ያካትታል። አንዴ የፕሮጀክቱ መረጃ ከተጋራ በኋላ የውጭ ግንኙነት ቢሮ በተለይ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ የፕሮጀክት ግንኙነት እና የስምሪት ዕቅድ (PCOP) ለመፍጠር ከፕሮጀክት ኃላፊ እና ከሌሎች ጋር ይሠራል። እያንዳንዱ ዕቅድ በአንቀጽ 6 ማህበረሰቦች ላይ ተጸእኖዎች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፣ እና የ WMATA የቋንቋ ተደራሽነት እቅድ መከተልን ያረጋግጣል።

በ 2015 የሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ከመተግበሩ ጀምሮ WMATA አሁን ሁሉንም የፕሮጀክት ግንኙነቶች እና ስምሪት ዕቅዶች አፈጻጸምን ልዩ በሆኑ የሪፖርት መለኪያዎች ይከታተላል።

እነዚህ የአፈጻፀም እርምጃዎች በ WMATA የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ሥርዓት (PPMS) ተብሎ በሚጠራ አዲስ የኦንላይን መሳሪያ ይከታተላል። መሳሪያው የ PPP ፕሮጀክቶችን ለመከታተል አዲስ መንገድ ያስገኛል እና ለ FTA ክትትል እና የማስከበር ሪፖርት አንድ ትልቅ ዳታ ቤዝ ይፈጥራል።

## 2014-2017 ግምገማ

የ WMATA 2014-2017 የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የአንድ ዓመት ባለ ብዙ ደረጃ ሂደት እና በአሁኑ ጊዜ በህዝብ ስምሪት እንቅስቃሴዎች ላይ በሚሠሩ ከተለያዩ ቢሮዎች እና ዲፓርትመንቶች የተውጣጣ ቡድን የተቀናበረ ነው፡፡

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ከተጀመረ አንስቶ ከ 35 በላይ የታቀዱ ፕሮጀክቶች የ PPP ሂደትን ተከትለዋል፣ አዳዲስ ብቅ ያሉ ዝግጅቶች፣ የማህበረሰብ ጉብኝቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ ክፍት ዝግጅቶች እና ሌሎች የተሳትፎ ስትራቴጂዎችን ጨምሮ ከ 1,000 በላይ እንቅስቃሴዎች ተከናውነዋል፡፡

በመጀመሪያው የሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የተገኙ ቁልፍ ግኝቶች አሁንም ለ 2017-2020 ይሠራሉ፡፡ እነዚህ ግኝቶች የመገናኛ እና ስምሪት ዕቅዶችን ለማሻሻል ጥቅም ላይ ውለዋል እና ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለብዙዎቹ ስኬቶች ጠንካራ መሠረት ጥለዋል፡፡

1. **የአንቀጽ 6 ህዝቦችን ለማግኘት፣ ወደ አሉበት ቦታ መሄድ።** አናሳ፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው እና **የ** LEP ህዝቦች የሚገኙባቸው — እንደ የመጓጓዣ ማዕከሎች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የገበያ ማዕከሎች እና ክብረ በዓላት - እነኚህን ህዝቦች ለመድረስ በጣም ውጤታማው ዘዴ ነው።

2. **ባሕላዊ ስሜታዊነትን ማሳየት።** አድማጭዎችዎን ይወቁና ወደ ተገቢው የ WMATA ሠራተኞች (የትምህርት ዓይነቶች፣ ባህል፣ እና የቋንቋ ችሎታ) ወደ ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች ያምጡ።

3. **ዝግጅቶችን ለመካፈል ምቹ ያድርጉ፣ እና የዝግጅቶቹን ፎርማቶች ከተካፋይ ቡድኖች ፍላጎቶች ጋር ያስተካክሉ።** የስብሰባ ፎርማቶች እንደ እያንዳንዱ ቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች ምርጫዎች መስተካከል አለባቸው – ይህም የአካል እና ምስልን ያካትታል። ልጆችን ለመጨመር መታሰብ አለበት፣ ለምሳሌ፣ ወላጆች የሚሳተፉበት የልጆች ፕሮግራሞችን ማካተት።

4. **ሰነዶችን መተርጎም እና ምስሎችን መጠቀም።** የመረጃ ጽሁፎች በሚሚለከተው ህዝብ ቋንቋ ምርጫ መኖር እና አድማጩን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምስል እና ቴክስት በመጠቀም ግልጽ የሆነ ለባህል ተገቢ የሆነ መልዕክት ማስተላለፍ።

5. **ሚዲያዎችን በተለያዩ ቋንቋዎች መጠቀም እና የማሰራጫ ዘዴዎችን መለዋወጥ።** ሰነዶች በተለያዩ የማሰራጫ ዘዴዎች እና ተሳፋሪዎች በሚያዘወትሩባቸው ቦታዎች እንደ አውቶቡስ፣ የአውቶቡስ ማቆሚያ፣ እና ሜትሮ ባቡር ጣቢያዎች መሰራጨት አለባቸው። በተጨማሪም፣ ማስታወቂያዎች መጓጓዣ ባልሆኑ ቦታዎች እንደ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ቤተ መጻህፍት፣ የምግብ መደብሮች እና የመኖሪያ አካባቢ መሰራጨት አለባቸው። በጋዜጣ ማስታወቂያ ማሰራጨት አሁንም ይሠራል እና ለብዙ ሰዎች የማህበረሰብ መረጃ ለማግኘት ተመራጭ መንገድ ነው።

6. **ግባዓቶችን ዕውቅና መስጠት እና መጠቀም።** የህዝብ ተሳትፎ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል በግልጽ መሆን አለበት።

7. **መሪ ዲፓርትመንት ያካተተ የህዝብ ተሳትፎ ድርጅታዊ መዋቅር ማቋቋም።** አንድ ዲፓርትመንት የህዝብ ተሳትፎን በበላይነት የሚቆጣጠር እና/ወይም የበርካታ ዲፓርትመንቶችን ተሳትፎ የሚያራምድ ሂደትን መከታተል አለበት።

8 **በተለያዩ ህዝቦች ላይ ግንኙነት እና ዕምነትን ለመገንባት ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር መሥራት።** እነዚህ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖች የአካባቢ ማህበረሰቦችን ይደግፋሉ፣ እና ለትራንዚት ኤጀንሲዎች አስፈላጊ የሆነውን እምነት እና የጋራ ጠቃሚ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት ከሚገኙ እጅግ በጣም ጠቃሚ መግለገያዎች መካከል ናቸው።

9 **ማስታወቂያውን ለማሰራጨት የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ።** ሌሎች ዘዴዎችን እንደ ለቤተሰቦች መረጃ ለማስተላለፍ የተማሪ ሪፖርት ካርድ የሚሰጥበትን ጊዜዎች መጠቀም ወይም በተመደቡ አካባቢዎች ከበሮ ወደ በር በመሄድ ማሰራጨትን የመሳሰሉ ዘዴዎችን መጠቀም።

10 **ቴክኖሎጂን በአግባቡ ይጠቀሙ።** ቴክኖሎጂ በህዝብ ተሳትፎ ቦታ ቢኖረውም፣ ከሌሎች የስምሪት ዘዴዎች ጋር መጠቀም ያስፈልጋል።

11 **ህዝቡ ስጋት ባለው ጉዳዮች ላይ ለ WMATA አስተያየት መስጠት እንዲችል ተደጋጋሚ የህዝብ መድረኮች ማዘጋጀት።** ይህ አስተያየት አሁን ያሉ በተለዩ ፕሮጀክቶች፣ ፕሮፖዛሎች እና ዕቅዶች ላይ አስተያየት መስጠት ዕድልን ይደግፋል።

## ለ 2014-2017 PPP ሀሳብ የተሰጠባቸው ዘዴዎች እና አፈጻጸም

በ FTA መስፈርቶች መሠረት፣ WMATA አናሳ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ (LEP) ማህበረሰቦችን ያሳተፉ ስትራቴጂዎችን አውጥቷል፣ ሁሉን የሚያሳትፍ ዘዴ እና ሥርዓቶች ፈጥሯል፣ ኤጀንሲው ተፈላጊውን ውጤት መድረሱን የሚከታተል የአፈጻጸም መለኪያዎች አዘጋጅቷል፡፡ የ2014-2017 PPP የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ፣ ብቁ እና የፌዴራል የህዝብ ተሳትፎን ውጤታማነት የሚያረጋግጥ አራት ዋና ስልቶች አሉት። በተጨማሪም፣ PPP አብዛኞቹ በመጀመሪያው ስትራተጂ የተካተቱ ተጨማሪ ሁለተኛ አስተያየቶች አሉት።

በ PPP በባለሥልጣኑ የተወሰውዱት የአሠራር ስትራተጂዎች በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ መሆናቸውን WMATA ለ FTA ተጠያቂ ነበር፡፡ በ 2014-2017 PPP የቀረቡ አራት ዋና ዋና ውሳኔዎች እና WMATA በሪፖርት ዓመቱ እነዚህን ውሳኔዎች እንዴት እንዳሟላ የሚገልጽ አጭር መግለጫ ከዚህ በታች ይገኛል፡፡

### የህዝብ ተሳትፎ የመሳሪያ ኪት እና የፕሮጀክት ግንኙነቶች/የስምሪት ዕቅድ

PPP እያንዳንዱን የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ ሠራተኞች የሚጠቀሙበት የፕሮጀክት ግንኙነት/ስምሪት ዕቅድ (Project Communications/Outreach Plan (PCOP) WMATA እንዲያዘጋጅ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም፣ በተለዩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ላይ ያተኮሩ ዘዴዎች ለመጀመር፣ ትክክለኛ እና ሰፋ ያለ የህዝብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ እና በ WMATA እና በማህበረሰብ ድርጅቶች (CBO) መካከል ዕውቀትን ለማስተላለፍ እንዲረዳ WMATA የማህበረሰብ ስምሪት ኮሚቴ እንዲያቋቁም PPP አስተያት ሰጥቷል፡፡

የውጭ ግንኙነት ቢሮ በ PPP 2014-2017 የተዘረጋውን መሳሪያ ወደ ድህረ ገጽ ተኮር፣ ለተጠቃሚ ምቹ የሆነ የፕሮጀክት መከታተያ መሳሪያ ለማስተላለፍ ከመረጃ ቴክኖሎጂ መምሪያ የድህረ ገጽ አፕሊኬሽን ቡድኖች ጋር በቅርብ ሠርቷል። ይህ የህዝብ ተሳትፎ አሠራር ዘዴ (Public Participation Management System (PPMS)) ተብሎ የሚጠራው መሳሪያ አስፈላጊውን የአፈጻፀም መለኪያ እና የእንቅስቃሴ ሪፖርቶችን ማስተላለፍ፣ ፕሮጀክት አስተዳዳሪዎች ከውጭ ግንኙነት ቢሮ ጋር በትብብር PCOP ማዘጋጀት እንዲችሉ እና ስነ ህዝብ መረጃ እና የተሳትፎ ሜትሪክ ግብአት ይፈቅዳል። በአቻ ኤጀንሲዎች የተሳካ ልምዶች ግምገማ መሠረት፣ ይህ መሳሪያ በህዝብ ተሳትፎ ትራፊክ የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል።

የ WMATA የመጀመሪያው የማህበረሰብ ድርጅት ስምሪት ኮሚቴ በ 2015 ዓ.ም. የተጀመረው በእኩል የቅጥር ዕድል ቢሮ (OEEO) አነሳሳሽነት ነበር። የመጀመሪያው የማህበረሰብ ድርጅት ስምሪት ኮሚቴ የሥራ ስብሰባ የተካሄደው ታህሳሥ 2015 ነበር። ከአካባቢው ማህበረሰብ ድርጅቶች ሰባት ተወካዮች ተገኝተው ኮሚቴውን እንዴት ወደፊት ማሳደግ እና ማስቀጠል እንደሚቻል አስተያየት ሰጥተዋል። ከመጀመሪያዎቹ ሁለት የዕቅድ ስብሰባዎች ጀምሮ፣ የ CBO ስምሪት ኮሚቴ ስብሰባዎች ከሜትሮ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ተደርገዋል። ቡድኑ በኢሜል ይገናኛል እና ግብአት ለመስጠት የፕሮጀክት መረጃን እና ዕድሎችን በየጊዜው ይቀበላል።

## የአፈጻፀጸም መለኪያዎች

PPP በተሳታፊ ዴሞግራፊ፣ የተሳታፊ አስተያየት እና የተሳታፊ ክትትል ላይ ያተኮረ ለእያንዳንዱ የህዝብ ተሳትፎ ፕሮጀክት እና ከእያንዳንዱ ፕሮጀክቶች እና ከማህበረሰብ ድርጅቶች የተገኘ ዓመታዊ ሰርቬይ ላይ ያተኮረ የአፈጻፀም ሪፖርት እንዲሰበሰብ አስተያየት ሰጥቷል።

2014-2017 የመጀመሪያ አስተያየት
2

በሥራ ላይ የዋለው በ 2015 አጋማሽ አዲሱ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማኔጅመንት ሲስተም (PPMS) ሲጀመር ነው። በ 2015 እና በ 2016 ዓ.ም. ከ 1,000 ተግባራት በላይ በ PPMS ሲስተም ውስጥ ክትትል ተደርጎባቸዋል። እነኝህ እያንዳንዱ እንቅስቃሴዎች ሁሉንም ተገቢ የገቢ ተሳትፎ መለኪያዎችን፣ የአስተያየት ዓይነቶችን እና ተጽዕኖ የደረሰባቸው ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንዴት ክትትል እንደተደረገባቸው ያጠቃልላል። በአዲሱ PPMS ሲስተም ክትትል በተደረገባችው ፕሮጀክቶች መሠረት፣ WMATA በሁሉም የአፈጻፀም መለኪያዎች 98 በመቶ ውጤት አግኝቷል።

## የህዝብ ተሳትፎ ሥልጠና

መሳሪያውን ስኬታማ፣ አንድ ዓይነት አጠቃቀም እና የአንቀጽ 6 የህዝብ ተሳትፎ መስፈርቶችን የሁሉንም ባለሥልጣን ግንዛቤን ለማረጋገጥ PPP በህዝብ ስምሪት ላይ የሚሠሩ የ WMATA ሠራተኞች መሣሪያውን እንዲጠቀሙ እና ሥልጠና እንዲሰጣቸው አስተያየት አቅርቧል።

2014-2017 የመጀመሪያ አስተያየት
3

PPP በሥራላይ ከዋለ ከግንቦት 2015 እስከ ነሐሴ 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አራት መርሐ-ግብሮችን በመምራት ከ 100 በላይ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች አሠልጥኗል። የሥልጠና ሰነዶች ለሁሉም ተካፋዮች ተሰጥቶ ነበር። ሰነዶቹ እና፡ ”የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ማስተዋወቂያ” ቪዲዮ ለ WMATA ሠራተኞች በሜትሮ ድህረ ገጽ ይገኛል።

## ማዕከላዊ የሕዝብ ተሳትፎ ጽ/ቤት

2014-2017 የመጀመሪያ አስተያየት
4

ከመሳሪያው በተጨማሪ፣ WMATA የህዝብ ስምሪቶችን ለማስተዳደር ማዕከላዊ ቢሮ እንዲያቋቁም PPP አሳስቧል። የውጭ ግንኙነት ቢሮ (EREL) ለያንዳንዱ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት/ዕቅድ ሠራተኛ፣ ሁሉንም ፕሮጀክት ላይ የተመሰረቱ የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን እና በ WMATA ውስጥ የህዝብ ተሳትፎን መከታተል እና ማስተባበር ኃላፊነት ተሰጥቶታል። እኩል የቅጥር ዕድሎች ጽ/ቤት (OEEO) ከማህበረሰብ ድርጅቶች (CBOs) ጋር ግንኙነቶች እና ስምሪት ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ተግባራት ተሰጥቶታል።

WMATA በውጭ ግንኙነት ቢሮ ወስጥ የህዝብ ተሳትፎ ፕሮግራሞች ቡድን አቋቋመ። ይህም ፕሮግራሙን ለማካሄድ አንድ ሠራተኛን ማዘዋወር እና በ2015 ፀደይ/በጋ ወቅት ሁለት ተጨማሪ ሠራተኞች መቅጠርን ያካትታል። የአሁኑ መዋቅር በውጭ ግንኙነት ዳይሬክተሩ ስር የህዝብ ተሳትፎ ፕሮግራሞች አስተዳዳሪ እና ሁለት የስምሪት ስፔሻሊስቶች/ልዩ ፕሮጀክት ኦፊሰሮችን ያካትታል።

ይህ ቡድን በ 2015 ዓ.ም. በሥራ ላይ ከዋለ ጀምሮ ከሌሎች የውስጥ ዲፓርትመንቶች ጋር በቅርብ በመሥራት ከ1,000 በላይ የታቀዱ ፕሮጀክቶች ግንኙነት እና የስምሪት እንቅስቅሴዎችን አቀነባብሯል። ሁለት ተጨማሪ ቦታዎች፣ የትርጉም ሥራ አስተባባሪ እና የፕሮጀክት አስተባባሪ ለመጨመር ተስፋ አለ፣ ሆኖም፣ በበጀት ችግር ምክንያት ለጊዜው በቆይታ ላይ ነው።

በተጨማሪም፣ እኩል የቅጥር ዕድል ቢሮ ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የሚያስተባብር አንድ አዲስ ሠራተኛ ቀጥሯል፣ እና በአሁኑ ሰዓት የማህበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎችን ለማነቃቃት እየሠራ ነው።

## ለወደፊቱ: 2017-2020 አስተያየቶች

ባለፉት ጥቂት ዓመታት WMATA ከህዝቡ ጋር የሚገናኝበት እና አስተያየት የሚሰበስብበት መንገዱን ለውጧል። በየሳምንቱ መጀመሪያ አዳዲስ ፕሮጀክቶች መከናወን እና በሺዎች የሚቆጠሩ ተሳፋሪዎች ላይ ተጽዕኖ መድረስ፣ WMATA ከደንበኞቹ፣ በተለይም ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑ ማህበረሰቦች ጋር የሚገናኝበት የበለጠ ቀልጣፋ መንገዶች ለማግኘት ይቀጥላል።

የአቻ ኤጀንሲዎችን ውጤታማ ልምዶች፣ የተሳፋሪ እና የሰራተኛ አስተያየትን፣ የሜትሮን አቅጣጫ በማስተዋል እና የበጀት ችግሮች ትምህርቶችን ከመገምገም ውጤት፣ ሁለት ሃሳቦች ቀርበዋል።

### ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው (LEP) ማህበረሰቦችን ለመድረስ የሚረዱ ስልቶችን እና ውስጣዊ ሂደቶችን ማስፋፋት።

2017-2020

አስተያየት

1

WMATA በ2014-2017 የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን በመጀመር የ LEP ማህበረሰቦችን ለመድረስ ትልቅ መሻሻል አድርጓል። ለሁሉም የታቀዱ ፕሮጀክቶች ግንኙነት እና ስምሪት ዕቅዶች ሲጀመሩ የሚመለከታቸው ህዝቦችን በማሰብ ሲሆን፣ ሁሉም የ LEP ክፍል ነበረው። የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ቡድኖች፣ የተተረጎሙ ምልክቶች፣ ማስታወቂያዎች እና ቁሳቁሶች ለሁሉም የታቀዱ ፕሮጀክቶች ተሳትፎ (PPP) እንቅስቃሴዎች መደበኛ ተግባሮች ሆነዋል። ይሁን እንጂ የሥራ ጫና እየጨመረ በመምጣቱ ለበርካታ ፕሮጀክቶች የትርጉም ሥራዎችን ለውጭ መስጠት፣ የሥራውን ጥራት መቆጣጠር እና ለ LEP ህዝቦች የግንኙነት እና የሚድያ መገናኛ ዘዴዎች አቅጣጫዎችን መገንዘብ አዲስ ስትራቴጂዎች ማስፈለጉ ግልጽ ሆኗል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እና አዲሱ በቋንቋ መገልገል ዕቅድን (Language Access Plan) ጨምሮ፣ WMATA የሚከተሉትን ስትራቴጂዎች ማሰብ አለበት፣

1. ግንኙነት እና ስምሪትን በተመለከተ ውስን ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦችን ከሚያገለግሉ የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነቶች መፍጠር እና አስተያየት መሰብሰብ። ይህም የማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮችን የተሻለ የሚያሳትፍ የቴክኖሎጂ እና ግንኙነት አማራጮችን መፈለግን፣ እና የቋንቋ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ግለሰቦች ለመገምገም ከማህበረሰብ ድርጅት ስምሪት ኮሚቴ ጋር መስራትን ያካተታል።
2. ሁሉንም የ PPP ትርጉሞችን እና የቋንቋ አስፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያስተናግድ የትርጉም ፕሮጀክት አቀነባባሪ ሠራተኛ ቦታ መፍጠር።
3. ለ PPP ፕሮጀችቶች በኮንትራት የሚሠሩ በጥሪ የሚያገለግሉ የትርጉምና የማስተርጎም ባለሚያዎች መቅጠር።

### ለመድረስ አስቸጋሪ ለሆኑ ማህበረሰቦች፣ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ እና የታቀዱ ፕሮጀክቶችን ለማዳረስ አዲስ እና የፈጠራ፣ በተለይም መረጃዎችን የሚያቆዩ መንገዶችን ማሰብ።

2017-2020

አስተያየት

2

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለተወሰኑ ህብረተሰቦች ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አዲስ የፈጠራ መገናኛ መሳሪያዎች ተሠርተዋል። ምንም እንኳን የአንቀጽ 6 ህዝቦችን ለመድረስ በአካል ስምሪት የበለጠ ውጤታማ መሆኑ ቢታወቅም፣ ኢንተርኔት ለማግኘት ረከስ ባለ ቴክኖሎጂ እና ፕሮግራሞች ምክንያት የዲጂታል መከፋፈል በላቀ ፍጥነት ይቀንሳል። በቴክኖሎጂ "ወደሚገኙበት ቦታ ለመሄድ" ሌሎች መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ። *Amplify*፣ የ WMATA የኦንላይን የማህበረሰብ ፖርታል የእነኝህን ዓይነቶች ዲጂታል የመጠቀም ፍላጎት አሳይቷል። ከዚህ በታች WMATA ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባው ሁለት ስልቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ተጽዕኖ በደረሰባቸው አካባቢ የሚገኙ ደንበኞችን መረጃ እና አስተያየት ለመሰብሰብ የጂኦ-አካባቢ ቴክኖሎጂ እንደ አማራጭ መጠቀም። ይህንን ቴክኖሎጂ፣ በሰርቬይም ሆነ በማስታወቂያዎች መጠቀም፣ ሰዎቹ ወዳሉበት ቦታ እንደመሄድ ይቆጠራል።

2. አስተያየቶችን ለመሰብሰብ አዳዲስ ዘዴዎችን፣ የኦንላይን የውይይት መድረኮችን፣ የንኪ ኪዮስኮችን እና የቲውተር አስተያየት መሰብሰቢያዎችን ጨምሮ መለየት።

## ማጠቃለያ

የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ሁሉን አቀፍ፣ ተጨባጭ፣ ትብብር እና ምላሽ ሰጪ የህዝብ ስምሪት ዝርዝር መመሪያዎችን ያካተተ አጠቃላይ ሰነድ ነው። ይህንን ዕቅድ በመፍጠር፣ WMATA የ FTA መስፈርቶችን ማሟላት ብቻ ሳይሆን፣ በተራማጅ የህዝብ ተሳትፎም መሪ ሆኗል።